# ሳትከፍላት አታልፍም

በህጋዊ መንገድ ፣ መንግስት ፈቅዶላቸው
መብራትና ውሃ ፣ አስገብቶላቸው
በአግባቡ ፣ ግብር ፣ እያስከፈላቸው
ህገወጥ የሆኑት ፣ ዛሬ ምን ታያቸው ?
እንዲህ ፣ በወገን ላይ ፣ የጨከኑባቸው
ወይስ ፣ እነ አብይ ፣ ሌላ ዓላማ አላቸው ? ።

ከሞቀ ጎጇቸው ፣ ከደራ ከኮራ
ገንብተው የኖሩ ፣ ወዳጅ ባልንጀራ
ወልደው ከሳሙበት ፣ ዘርተው ከቃሙበት
ጎጆውን በላዩ ፣ ድንገት ሲያፈርሱበት
ህፃን ሽማግሌ ፣ ደካማ አዛውንቶች
አራስ ቤት ፣ የተኙ ፣ የሚያጠቡ እናቶች
በግፍ ተበትነው ፣ ሜዳ ላይ ሲጣሉ
ሰባተኛው ንጉስ ፣ እንዲያው ምን ይላሉ ?

የንጉሱ ልጆች ፣ መቼ በረዳቸው
መቼስ ተንገላቱ ፣ መች ፀሀይ መታቸው
የንጉስ ልጅማ ፣ ሞልቃቃ ቅንጡ
ቤት አልባ ፣ አልሆኑ ፣ የሚበላ አላጡ
ብስሉን ከጥሬ ፣ ይብሉ እያማረጡ
አለርህራሄ ፣ ደሃን እየቀጡ ።

እድሜ ላባታቸው ፣ ሰባኪ ፓስተሩ
ደሃ እያስለቀሰ ፣ ለሚል ተፋቀሩ
አስመስሎ አዳሪ ፣ ወንጌል ተንተርሶ
እርካታን የሚያገኝ ፣ ደሃን አስለቅሶ
ለምን ያለቅሳሉ ፣ እሱ እስካለ ድረስ
በሰፈሩት ቁና ፣ መሰፈር እስኪደርስ ።

ዘመነኛ ንጉስ ፣ ወሬ እያጣፈጡ
ደሃውን ከቀዬው ፣ ነቅለው እያወጡ
የሃሰት ሰባኪ ፣ ወሬ ፣ ምላስ ጌጡ
ህዝብን ፣ ደንቆሮ አርገው ፣ በሰው ሲያላግጡ
ኦሮሞ ያልሆነውን ፣ ካገር እያስወጡ
አልሰማሁም አሉን ፣ ጭራሽ አይን አወጡ
ደሃን አስጨነቁት ፣ ሱሪ ፣ ባንገት አውጡ
የተዘመረለት ፣ ይሄው ነበር ለውጡ ።

ህዝቡ ግራ ገባው ፣ ሆነበት እንግዳ
መረዳት አልቻለም ፣ ጭራሽ ሆኗል ባዳ
በነጋ በጠባ ፣ በጣቃው ፣ ቀደዳ
አገር አላዳነ ፣ ወይ ፣ አልከፈለ ዕዳ
እንደኢህ ነው መሰለኝ ፣ በበሽሻ አራዳ ።

ባንተ ያለቀሱት ፣ አዛውንት መነኩሴ
ቀና ብለው ሰማይ ፣ ያሉት ለስላሴ
አስበኝ አይደለም ፣ ምህረት ለነፍሴ
ላንተ እድሜም ፣ ልመና ፣ አይደለም ውዳሴ
ሲወጋህ ታውቃለህ ፣ የመቅሰፍት አንካሴ
ሳትከፍላት አታልፍም ፣ ፀጉር ከምላሴ ።

ታዛቢው

March 13, 2019